# ቼ በሉኝ ባንቀልባ

(ከዓሊ ሁሴን)

ይህን በሽኮኮ

ያንንም በአንቀልባ፣

ጠዋተና ማታ

አዝዬ በጀርባ፣

ዋና አከረካሪዬ

ሆነና ሰለባ፣

አንድ እርምጃ ወደፊት

ሁለት ወደ ሁዋላ፣

ጉዞዬ እየሆነ

አቅሜም እየላላ፣

ያሽካካል ጠላቴ

ወጣት፣ ሽማግሌ፣ እንቡጥ እየበላ!

ሚስቴን፣ ልጄን ደፍሮ

ሰብዕናዬን ልሶ፣

አገሬን ቆራርጦ፣

ሰንደቄን ብጣጥሶ፣

ይዞ ጮቤ ይረግጣል፣

ጠላት ደስ ብሎት

ትግሌ ባለ አንቀልባ፣

እንደሆነ ገብቶት።

የትኛው ሊሳካ

ምኑን ግብ ልንመታ፣

ምንኛ ሊቁዋጠር

የትኛው ሊፈታ፣

የመከራችን ዶፍ

እምን ቀን ሊያባራ፣

ጨለማው ሊያበቃ፣

ድፍርሱ ሊጠራ፣

ታጋይ ተበራክቶ፣

ቼ በሉኝ ባንቀልባ፣

አንድ እርምጃ ወደፊት

ሁለት ወደ ሁዋላ፣

ጉዞው ውጤት አልባ።